# ደንብ IKA-RA፥ ስለ ውጤት አሰጣጥ እና ሪፖርት ማድረግ ማሻሻያ
# 2025-2026 የትምህርት ዓመት

**ለምን?**

| ተማሪዎች ጠንክረው እንዲሠሩ ለማበረታታት እና ተጠያቂነትን ለማስፈን | በተለያዩ ትምህርት ቤቶች ያለውን የተራራቀ ልዩነት ለማጥበብ | የሚጠበቁ የትምህርት ውጤቶችን ግልጽ ለማድረግ |
|---|---|---|

**የተለወጠው ነገር ምንድነው?**

- **የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት/ኮርስ የውጤት አሰጣጥ ስሌት፡-** ከ 6ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ተማሪዎች በሙሉ አዲስ አይነት የማጠቃለያ ውጤት አሰጣጥ ስሌት ይተገበራል። ከ 2025-2026 የትምህርት አመት ጀምሮ፣ የመጨረሻው የኮርስ ውጤት የሚወሰነው ከእያንዳንዱ የማርክ መስጫ ወቅት በቁጥር የሚሰጡ ውጤቶችን አማካይ ውጤት በማስላት ነው። መምህራን በፊደል የሚጻፈውን የመጨረሻውን ውጤት ለመወሰን ከዚህ በኋላ የውጤት መስጫ የስሌት ሠንጠረዥ አይጠቀሙም።
    - በሴሚስተር ለሚጠናቀቁ ኮርሶች፡-የመጨረሻውን ውጤት ለማስላት ከሁለቱም የማርክ መስጫ ወቅቶች አሃዛዊ ውጤቶችን ድምር ለሁለት በማካፈል አማካኝ ውጤቱ ይወሰዳል።
    - የሙሉ አመት ኮርሶች፡- የመጨረሻው ውጤት የሚሰላው የአራቱም በቁጥር የተጻፉ የማርክ ውጤቶችን በመደመር እና ለአራት በማካፈል አማካዩ የማጠቃለያ ውጤት ይሆናል።
    - የኮርስ ማጠናቀቂያ (EOC) ፈተና ውጤት፡- የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE) በባዮሎጂ እና NSL Gov’t የመጨረሻ የኮርስ ምዘና የሴሚስተር B ውጤት 20% ነው።

- **የማርክ መስጫ ክፍለጊዜዎች (MP) 2 እና 4 ማጠቃለያ ምዘናዎች፡-** ለሚከተሉት ትምህርቶች ዲስትሪክት አቀፍ የማጠቃለያ ምዘናዎች ይተገበራሉ፡ ENG 6-8/ENG 6-8 for EMLs፣ ENG 9/ ENG 1 for EMLs፣ ENG 10/10 12፣ Algebra 1 A/B፣ Algebra 2 A/B፣ Pre-calculus A/B አሥር ፐርሰንት MP 2 እና MP 4 ውጤት 10% ይቆጠራል።

- **የሪፖርት ካርዶች፡-** አዲሱን የተማሪዎችን የትምህርት አፈጻጸም ሪፖርት ለማድረግ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን የሪፖርት ካርድ ይሻሻላል።

- **ድጋሚ ግምገማ፡-** በሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ኮርሶች፣ መምህራን በሁሉም የኮርሶች ምድብ በእያንዳንዱ ማርክ መስጫ ወቅት ለተማሪዎች ቢያንስ ሁለት ዙር የመገምገም እድሎችን ይሰጣሉ። ለሚከተሉት ምዘናዎች እንደገና ግምገማ አይሰጥም፡- የኮርስ ማጠቃለያ ምዘናዎች፣ የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ ምዘናዎች፣ አስፈላጊ የዲስትሪክት ምዘናዎች፣ የሴሚስተር ማጠቃለያ ምዘናዎች፣ የመጨረሻ የምርምር ጽሑፎች፣ ፕሮጀክቶች ወይም ጽሑፎች፣ እና የማጠናቀቂያ ፕሮጀክቶች ወይም አፈፃፀሞች ዳግመኛ ምዘና አይሰጣቸውም።

- **የመጨረሻ ቀናት እና ቀነገደቦች፡-**
    - ከመጀመሪያው የማስረከቢያ ቀን በኋላ የመጨረሻው ቀነገደብ ከ 10 የትምህርት ቀናት በላይ ሊሆን አይችልም።
    - ወቅታዊ የውጤት ሪፖርት ለመስጠት አስቸጋሪ ስለሚሆን፣ እያንዳንዱ የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ ከማብቃቱ በፊት እስከ መጨረሻዎቹ 5 የትምህርት ቀናት ዘግይቶ የሚቀርብ ስራ ተቀባይነት አይኖረውም።

- **50% መስጠት፡-** የተማሪ የስራ ውጤት ወይም ትክክለኛነት ምንም ይሁን ምን መምህራን በሚገመግሟቸው ተዛማጅ ምዘናዎች ላይከ 50% በታች መስጠት የለባቸውም። መምህራን ድጋፍ መስጠት እና ጧልቃ ገብተው በማስተማር እገዛ ማድረግ ይቀጥላሉ።

- **የተማሪዎችን የስራ ውጤት መልሶ መስጠት፡-** የተማሪዎች ሥራ ውጤት ከተሰጠበት በኋላ 10 የትምህርት ቀናት ውስጥ ለተማሪዎች ይመለሳል።